# አገር እንዴት ሰነበተች?  ቁጥር 6

የካቲት 12 ቀን 2014ዓም(19-02-2022)

ካለፈው ስርጭታችን ወዲህ በአገራችን ብዙ ነገሮች ተከስተዋል፣ታይተዋል፣ተሰምተዋል።በሳምንቱ ውስጥ የተከናወኑትን ሁሉንም ለማንሳትና ለመተቸት ጊዜው ስለማይበቃ  የዛሬው የአገር እንዴት ሰነበተች ዝግጅታችን ዋና ዋና ናቸው በሚላቸው እርእሶች ላይ ብቻ የሚያተኩር ይሆናል።

በወያኔና በኦነግ ፋሽስታዊ  አሸባሪ ቡድኖች የሚፈጸመው ግድያ፣ጭፍጨፋና ውድመት በስፋት እዬቀጠለ ነው።መንግሥት ተብዬው ተረኛ የኦሮሙማ ቡድን ለአሸባሪዎቹ የቀጥታና ስውር ድጋፉን እዬቸራቸው፣ ለተበዳዩ ሕዝብ ግን ሳይደርስለት ያዞ እምባውን እዬረጨ መሸንገልና ማጭበርበሩን ቀጥሎበታል።

የዓለም ማህበረሰብ የተባለውንም እንዲሁ  ኢትዮጵያ የሰላምና የእድገት ጉዞ ላይ ነች በማለት የሚያውቁትን እውነታ  ለመሸፋፈንና ለማጭበርበር ያልሞከረው ሙከራ የለም።የሕዝቡ መኖሪያ ቤት እዬፈራረሰ ተፈናቅሎ የድንኳን መጠለያ እንኳን ባጣበት ሁኔታ ላይ እያለ፣በርሃብና በበሽታ እዬተሰቃዬ የእርዳታ ያለህ ሲል መንግሥት ተብዬው ቡድን ከሚዘርፈው የተረፈውን ያገሪቱን እንጥፍጣፊ ሃብት በፎቅና የመዝናኛ (ፓርክ) ግንባታ ላይ በማፍሰስ ላይ ተሰማርቷል።ግንባታ ለአንድ አገር አስፈላጊ መሆኑ ቢታመንበትም ቅደም ተከተልና አስፈላጊነቱን ያላገናዘበ ግንባታ ግን ለሙስናና ለዘረፋ ሽፋን ሲባል የሚደረግ እንጂ የሚሰጠው ጥቅም ከጊዜው ጋር የተጣጣመና የተንሰራፋውን መጠነ ሰፊ ችግር የሚቀንስ  አይደለም።ከግንቡ ሥርና ጀርባ  ላስቲክ ለብሰውና በጭርንቁስ ሰፈር የሚኖሩትን እንዲሁም በከተማም ሆነ በገጠሩ የፍትሕ ያለህ የሚሉትን ብዙሃኑን ደሃ ዜጎች አለማዬትና አለማሰብ ብቻ ሳይሆን በነዋይና ሥልጣን ፍቅር የሚመጣ እብደት ነው።

ለዚህ ግንባታ፣ወይም ለዚህ እድሳት ይህንን ያህል ቢሊዮን ብር ወጣ የሚሉት ወሬ ተደጋግሞ ሲሰማ የቢሊዮንን ትርጉምና መጠን ከማሳነሱም በላይ የገንዘቡን ክብደትና የመግዛት አቅም ያሳጣዋል።ለኑሮ ውድነትም አንዱ ምክንያት የሆነው ይኸው እንግዳ ቁጥር ነው።የብድርና የእርዳታ ያለህ የሚለው መንግሥት የሚያባክነው ገንዘብ ከዬት እንደመጣ ሲያስቡት ግራ ያጋባል።አጨብጫቢውም ለሚመራው የተቀናጣ ኑሮ  ምንጩ ምን እንደሆነ አይታወቅም።በውጭ አገር የሚኖረው ነው እንዳይባል የውጭ አገሩ ኑሮ የሚታወቅ ነው።የመንግሥትና የድርጅቶች እጅ ሳያዩ ሠርቶ ኑሮን አሸንፎ ማደር ለጥቂቶች የታደለ ጸጋ ነው።አብዛኛው ከመንግሥት እርጥባንና እርዳታ የተላቀቀ አይደለም። የፈረንጅ አገር ለማኝ ነው ማለቱ ይገልጸዋል።ለከፍተኛ ትምህርት የታደለው እጅግ በጣም ጥቂቱ በተማረው መስክ ተቀጥሮ ከበቂ በላይ ደመወዝ እዬበላ ይኖራል፤አንዳንዱም በግል የሱቅና የምግብ ቤት ንግድ ላይ ተሰማርቶ ኑሮውን ይገፋል። በአገር ቤት ቤትና ንብረት ለመያዝ የቻሉትም እነዚህ ከፍተኛ ደመወዝ ያላቸውና በተሳካ የንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩት ናቸው። ገንዘብ መያዛቸው ብቻም ሳይሆን በሥልጣን ላይ ላለው ጎሰኛ መንግሥት ታማኝና ደጋፊ የመሆንም ግዴታ ያሟሉ መሆን ይጠበቅባቸዋል፤ናቸውም።

ከሳምንቱ ትኩረት ከተሰጠው መካከል ባለፈው እሁድ በአዲስ አበባ ከተማ ከአምስት ዓመት በፊት ተጀምሮ የተጠናቀቀው ባለ53 ፎቅ  የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ  ህንጻ ምረቃ ነበር።ይህ በቻይናዎች የተገነባ  በርዝማኔው የመጀመሪያ ነው ተብሎ የተነገረለት ትልቅ ሕንጻ ስንት እንደፈጀ በእርግጠኛነት መናገር ባይቻልም ምክንያቱም የሂሳብ ምርመራ ሊያስከትልና የሙስናና የስርቀቱን ምስጢር ሊያጋልጥ

ስለሚችል በደፈናው ብዙ ቢሊዮን ብር  ወጣበት እንደሚባል ከዘመኑ የወጭ መጠን አንጻር መገመት አያቅትም።ሕንጻውን ለመሥራት መሠቱን ያስቀመጠው አሁን በእስር ላይ ያለው በረከት ስምኦን የተባለው ቀንደኛ የህወሃት መሪ እንደነበረና ስሙም በመሰረት ድንጋዩ ላይ ሰፍሮ እንደነበር ተገልጿል ፣ሆኖም ግን አሁን ወያኔ ተወግዶ እሱም  በእስራት ላይ በመሆኑ ስሙ ከመሰረት ድንጋዩ ላይ ተፍቆ ተነስቷል።የማን እንደሚቀመጥበት ወደፊት የምናዬው ይሆናል እንጂ ከነፍቅፋቂው  ይቀራል ብለን አንገምትም።የአብይ አህመድ ወይም የአንዱ ባለጊዜ ስም ቢለጠፍበት የሚያስገርም አይሆንም።ታሪክ በታሪክነቱ መቀመጥ አለበት እንጂ ታሪክ ያልሠሩት የሚነጥቁና ባለታሪክ የሚሆኑበት አሠራር ስለተለመደ ሊወገዝ ይገባል።ምንም እንኳን በበረከት ስምኦን መልካም ፈቃድና ውሳኔ የተሠራ ባይሆንም ሥርዓቱን ወክሎ ያሰቀመጠው የመሠረት ድንጋይ በመሆኑ መልካምም ሆነ መጥፎ ሥራ ተተኪው ትውልድ ማወቅ አለበት።ንብረትነቱም የሕዝቡ ስለሆነ ሕዝቡ የማወቅ መብት አለው።

ማንሳት ያለብን ቁም ነገር  እውነት በአገሪቱ በተለይም በአዲስ አበባ ውስጥ ያሉት ባንኮች ለገንዘብ ዝውውሩ በማነሳቸው  ብዙ ቢሊዮን ያህል ገንዘብ አውጥቶ ይህንን የሚያክል የባንክ ሕንጻ መገንባቱ ለምን አስፈለገ?ተገቢ ነው አይደለም ?ያገሪቱን አቅምና የሕዝቡን ፍላጎት ያገናዘበ ነወይ? የሚሉትን ጥያቄዎች ነው። መልሳችን የኦሮሙማው ተረኛ ካለው የወደፊት ከተማዋን የመዋጥ እቅድ በኢትዮጵያ በተለይም በአዲስ አበባ ሕዝብ ኪሳራ ጓዳውን የመሙላቱ ቅድመ ዝግጅት ነው ብለን እናምናለን።በመክፈቻ ምረቃው ላይ የተገኘው አብይ አህመድ ባደረገው ንግግር ከባንኩ ጋር ያልተያያዘ የጨልሌዎች ታሪክ አንስቷል፤ የሚገርመው ግን ይህንን ሲል  የባንኩ አመራርና የቦርድ አባል ያደረጋቸው የኦሕዴድ ጨልሌዎች  ዙሪያውን ከበውት ነው። ትችት ያስነሳው ንግግሩ ግን የውጭ አገር ባንኮችም ለመግባት ተፈቅዶላቸዋል ፣ይመጣሉ ማለቱ ነው።ይህም ነጮቹን ለማስደሰት ከሚጠይቁት ጥያቄ ውስጥ አንዱ ስለሆነ ነው። የሚመጡ ከሆነ በአገሪቱ ባንኮች ላይ ብሎም በአገሪቱ ኤኮኖሚ ላይ ሊያደርሱ የሚችሉት ጉዳት በቀላሉ የሚገመት አይደለም።የውጭ ምንዛሬ በእጃቸው ስላለ የብድሩን ሜዳና የወለድ መጠን ወሳኞቹ እነሱ ይሆናሉ ማለት ነው።ካለተፎካካሪ የሚሽመደመደው የአገራችን የባንክ ሰንሰለት በነዚህ የውጭ አገር ባንኮች ተገፍቶ ከጨዋታ ውጭ ይሆናል ማለት ነው።እንኳንስ ዘንቦብሽ እንዲያውም ጤዛ ነሽ እንዲሉ በውጩ ተጽእኖ ጭራሽ ይለይለታል ማለት ነው።የአገር ኤኮኖሚ የሚንቀሳቀሰው በአገር በቀል ዘርፍ መሆኑ ይቀርና፣ የአገር ሃብት በውጭ አገር ባንኮች ቁጥጥር ውስጥ ወድቆ ይበዘበዛል ማለት ነው። የብሩም ምንዛሬ ተመን በነዚሁ የውጭ ባንኮች ውሳኔ ይሆናል ማለት ነው።የእጅ አዙር አገዛዝ አንዱ መንገድ ብሔራዊ ኤኮኖሚ እንዳያድግ መቆጣጠር ነው። ለአብይ አህመድና ለቡድኖቹ ግን ዋናው የሚያሳስባቸው በሠሩት ወንጀል በምዕራባውያኑ አለመጠዬቅ ስለሆነ የተጠዬቁትን ከማድረግ ወደኋላ አይሉም።መስሏቸው እንጂ አይቀርላቸውም።ምዕራባውያኑ ቀን ጠብቀው ያሰቡትን ያደርጋሉ፤ ኢትዮጵያን ብሎም አፍሪካን  ከማንበርከክ ዓላማቸው አይመለሱም።ለዚያ ጥርጊያ መንገድ፣ የአፍሪካንና የአውሮፓን ግንኙነት ለማሻሻል በሚል ሽንገላ ከመቶ ሃምሳ ሚሊዮን ኤሮ በላይ መድበናል፤እንገናኝና እንመካከር ሲሉ የአፍሪካ መሪዎችን ቤልጅዬም ከተማ ብራሰልስ ጠርተው አነጋግረዋል።የአፍሪካ መሪዎችን ደካማ ጎን ስለሚያውቁ ገንዘቧን የመሳቢያ ከረሜላ ማድረጋቸው የተለመደ ነው።ከተገኙት መሃል አብይ አህመድም አንዱ ነበር።ምን እንደተነጋገረ ባይታወቅም ከብዙ የአውሮፓ መሪዎች ጋር በግል ተገናኝቶ ተነጋግሯል።ሊነጋገርበት የሚችለውን ስናስብ ከፋሽስቶቹ ከወያኔና ከኦነግ አሸባሪ ሃይሎች ጋር ስለሚያደርገው የስምምነት ድርድር፣በአባይ ግድብ ዙሪያ ከግብጽና ከሱዳን ጋር የስምምነት ውል መፈራረም እንዳለበት በያዙት አስገዳጅ አቋም ላይ  ሊሆን ይችላል የሚል ነው።ከዚህ ውጭ ምዕራባውያንን የሚያሳስባቸው ጉዳይ አይኖርም። አብይም ያሉትን ከመቀበል አይመለስም።በተግባርም እዬገለጸው ነው።

የባንክን ነገር ካነሳን ይኸው ይሉኝታ ቢሱ ተረኛ የኦሕዴድ አነግ ቡድን ያገሪቱ ዋና ዋና ተቋማት፣ የኢትዮጵያ አዬር መንገድን ጨምሮ ሒሳባቸውን በኦሮሚያ በሚባለው ባንክ ውስጥ እንዲያነሸራሽሩ ግዴታ ተጥሎባቸዋል።ይህ ባንክ የአገር ውስጥና የውጩን የገንዘብ ዝውውር በስፋት እንዲቆጣጠር ተደርጓል።ቀደም ሲል አዋሽ ባንክና አዋሽ ኢንሹራንስ የተባሉት ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ የኦሮሞ ተወላጆች የሚቆጣጠሯቸው ሲሆን ለረጅም ጊዜ ከአሜሪካ ባንክ (Bank Of America)ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዳላቸው የሚያውቅ ያውቀዋል።እነዚህ ሁለቱ ባንኮች አንድ አካል አንድ አምሳል ሆነው ለኦሮሙማው አገረ መንግሥት የኤኮኖሚ የጀርባ አጥንት ሆነው ያገለግላሉ። እንደ ኦሕዴድ ከሆነ ከጊዜ በኋላ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሚለውም ስሙ ተቀይሮ የኦሮሚያ ንግድ ባንክ ላለመባሉ ዋስትና የለም።የሁሉም ነገር መጠሪያ ያው በኦሮሙማው ውሳኔና ፍላጎት ስለሆነ እስከአሁን የተሄደበት መንገድ አመላካች ነው።ኢትዮጵያን ለማፍረስ የተነሳ ቡድን ያንን ከማድረግ ይቆጠባል ተብሎ አይጠበቅም።

ባለፈው ሳምንት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሲኖዶስ አሳሳቢነት ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጋር ለመነጋገር በተያዘው ቀጠሮ መሰረት ከንቲባዋ ከባልደረቦቿ ጋር ሆና በመንበረ ፓትሪያርኩ የስብሰባ ቢሮ ተገኝታለች።በዚህ ስብሰባ ላይ በሲኖዶሱ በኩል የተነሱት የመስቀል አደባባይና የጃንሜዳ የባለቤትነት ጥያቄና በጥምቀቱ ክብረበዓል በዋይበላ ማርያም የንግሥና ቀን በንጹሃን ምእመናን ላይ በተፈጸመው የደም ማፈሰስ ወንጀል ላይ በተሳተፉት የመንግሥት የጸጥታ ሃይሎች ላይ ስለሚወሰደው ሕጋዊ እርምጃ ነበር። በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ለመስጠት ከሁለቱም በኩል የተውጣጣ ኮሚቴ ተመስርቶ እንዲያጠናው ተስማምተው ተለያዬተዋል።አሻፈረኝ ብላ ስታስቸግር የነበረችው ከንቲባ ከሲኖዶሱ መምበር ላይ ለመቅረብ ያስገደዳት የገጠማት የሕዝቡ ተቃውሞ እንጂ ከበጎ ፍላጎቷ እንዳልሆነ ሁሉም ያውቀዋል።አዎ! ሕዝብ ከተነሳ የማይቻል ነገር ላለመኖሩ ይህ ማሳያ ነው።ለሌላውም አገራዊ ጥያቄ ሕዝቡ ተባብሮ እንዲነሳ አሁንም ልናሳስብ እንወዳለን።

አሁን ላይ ግን ከሌላ አቅጣጫ ጃንሜዳም ሆነ መስቀል አደባባይ የማንም የሃይማኖት ተቋም ንብረት ሳይሆን የሁሉም ንብረት ነው የሚል የፌስቡክስ ዘመቻ በመሰራጨት ላይ ይገኛል።ይህንን የሚቀሰቅሱት እነአዳነች አበቤ ያሰማሯቸውና ጸረ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አቋም ያላቸው ለመሆናቸው እርግጠኛ ሆኖ መናገር ይቻላል።ዝም ከተባለ አቅጣጫውን እንዳይቀይር ያሰጋል።የኮሚቴውን ጥናትና ውሳኔ ወደፊት የምናዬው ቢሆንም ቤተክህነት በአቋሟ ከጸናችና የሕዝቡም ትግል ከተጠናከረ ክርክሩን ሊያሸንፉ ይችላሉ።የሚያሳስበው ግን መሬትን የመንግሥት ንብረት ያደረገው ሕገመንግሥት እስካለ ድረስ ግለሰብም ሆነ ተቋማት የቀድሞ ይዞታው ባለቤት የመሆኑ ዕድሉ የመነመነ ነው።በዚያ ላይ የኦሮሙማው ሁሉም የኛ! ህሳቤ ሲጨመርበት ነገሩን የበለጠ ውስብስብ ያደርገዋል ብለን እንሰጋለን።

የትግራይ አፈንጋጭና አሸባሪ ቡድን ህወሃት ተሸክሞት የኖረውን የመገንጠል ዓላማ እውን ለማድረግ መንደርደሪያ ያደረገው የትግራይ ቤተ ክህነትንና የሙስሊሙን መጅሊስ ከአገር አቀፉ ሲኖዶስና የሙስሊም መጅሊስ ለያይቶ ማወጁ ነው።የትግራይን ፓትሪያርክ በግብጽ ለማሾም ግንኙነት እንደጀመረ ማስረጃዎች እዬወጡ ነው።የትግራይ ሕዝብ ይህንን ብሔራዊ ኩራት የሆነ ታሪኩን ጥሎ ለግብጽ ፈርኦናውያን ጊዜ ባርነት ለማደር ይስማማል ብለን አንገምትም። ወያኔ ካለው ጸረ ሃይማኖት አቋሙ ለሁለቱም ሃይማኖቶች አስቦ ያደረገው ሳይሆን ነጥሎና አዳክሞ ለማጥፋት እንደሆነ መዘንጋት የለበትም።በተለይም ሙስሊሙ ማህበረሰብ በአጼ ዩሃንስ ዘመነመንግሥት ጊዜ በሃይማኖቱ ምክንያት መሬቱን እንደተነጠቀና እንደተሰደደ የሚካድ አይደለም።በወያኔ ጊዜም እስከቅርብ ድረስ ምናልባትም እስከዛሬዋ እለት በአክሱም የሚኖር ሙስሊም መስጊድና የመቃብር ቦታ ተንፍጎት ለብዙ እርቀት ጉዞ የተጋለጠ መሆኑ የማይታበል ሃቅ ነው።በሌላው ቦታ ጽላትና ቁርዓን ያዋረደ፣መስጊድና ቤተክርስቲያን

ያቃጠለ ቡድን በትግራይ ውስጥ በክብር ይይዛቸዋል ማለት ከንቱ ምኞት ነው።የእምነቶቹ ተከታዮች የትም ቦታ ቢሆን በእምነታቸው ላይ የተሰነዘረን ድፍረትና ጥቃት የእኔ ጥቃትና መደፈር ነው ብለው ሊያስቡት ይገባል። ስለሆነም የሁለቱም ቤተእምነት ምእመናን እጅ ለእጅ ተያይዘው ይህንን እኩይ ቡድንና እርምጃውን ሊከላከሉት ብሎም ሊያሶግዱት ይገባል።ያንን ካላደረጉ ነጣጥሎ ጅብ የበላቸውን በሬዎች ታሪክ መድገም ይሆናል።

የወያኔ እብደት በዚህ ብቻ አይቆምም፣ ያለ የሌለ ሃይሉን በመሰብሰብሰብ በያቅጣጫው ጦርነት ለመክፈት አቅዶ በመንቀሳቀስ ላይ ነው።በኢትዮጵያ ውስጥ በአማራውና በአፋሩ ላይ የሚያደርሰው ጥቃት እዬጨመረ፣ከኦነግ አሸባሪ መሰሉ ጋር በመተባበርም ወረራ በማካሄድ ትልቅ ጉዳት አድርሷል፤ በማድረስም ላይ ነው።በኤርትራም በኩል እንዲሁ ከተቃዋሚው ጋር ሆኜ ኢሳያስ አፈወርቂን አሶግጄ ታላቋን ትግራይ ትግርኛ ሃገር እመሰርታለሁ ብሎ እዬዳከረ ነው። ይህንን ይበል እንጂ ለኤርትራ ስደተኞች እርህራሄ አላሳዬም።ከአበርገሌ ወጣ ብሎ በሚገኘው የኤርትራ ስደተኞች ጣቢያ በመግባት ጥቃት አድርሶ 25 ገሎ ሌሎቹን ከ10-15 ዓመት ዕድሜ ያላቸውን ታዳጊ ሴት ልጆች ደፍሮና አፍኖ ወደ መቀሌ መውሰዱን ቆስለው ያመለጡ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያው አሕዴድ መራሹ ኦነግ መንግሥት ኢትዮጵያን በማፈራረሱ ላይ ለወያኔ ቡድን ተባባሪው ቢሆንም ኢሳያስ አፈወርቂ ግን ለዚህ ለወያኔ ምኞት ይንበረከካል ተብሎ አይታሰብም።ምንም እንኳን የኤርትራ ሕዝብ የኢሳያስ መንግሥት አገዛዝ ቢያንገሸግሸውም ለወያኔ መራሹ ተቃዋሚ መልካም አስተያዬት ይኖረዋል ተብሎ አይጠበቅም።ለኤርትራም ሆነ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅምና ዘላቂ ሰላም የሚያዋጣው ሌላው ቢቀር በፌዴሬሽን መልክ መተሳሰሩ ነው እንላለን።

በስማቸው የሚነገደው የትግራይና የኦሮሞ ማህበረሰብ ተወላጆች ህወሃትና ኦነግ የሚያደርጉትን ጭፍጨፋ፣ ሕዝብን አለያይቶ በጠላትነት ማሰለፍና አገር የማፍረስ ሴራ ሊቃወሙት ይገባል። በዝምታ ካለፉት በታሪክ ተጠያቂ ይሆናሉ።በያዙት ከቀጠሉ እነሱንም ጨምሮ ሁሉም አገረቢስ ሆኖ ስደተኛ የመሆኑ ዕድሉ ከፍተኛ ነው።

ባለፉት ቀናት ውስጥ የተሰራጨው ሌላው ጉዳይ በሶማሌ ክልል በተባለው ያገራችን ክፍል በሙስጠፌ ሙሃመድ አስተዳደር ላይ ተቃውሞና የመገልበጥ ሙከራ ተደርጎ መክሸፉን ነው።የፌዴራል መከላከያ ሃይልም መግባቱ የተሰማ ቢሆንም ከመንግሥት በኩል ግን የተሰጠ ማብራሪያ የለም።በክህደትና በዘረፋ ውስጥ የተዘፈቀው የብልጽግና ቡድን መውደቂያው ሲቃረብ ከዚህ አይነቱ ውስጣዊ ቀውስ ይትርፋል ተብሎ አይጠበቅም።የኦነግ ኦሮሙማው ዘራፊ ከሶማሌ ክልል መሬት ቦጭቆ ለመውሰድ አሰፍስፎ ይገኛል።አልፎ አልፎም ጦርነት ከፍቶ ሕዝቡን እያመሰ መሆኑ ተሰምቷል።በዚህ ቀውስ ውስጥ የሚዳከረው የክልሉ ብልጽግና ስብሰባ በማካሄድ ላይ መሆኑ ተሰምቷል።

ፊታችንን ወደ አማራው ክልል ስንመልስ አሁንም ወያኔ በያዘው የወሎ ክ/ሃገር መሬት ላይ አስተዳደሩን ዘርግቶ ሕዝቡን የቁም ስቃይ እያሳዬው ሲሆን፣ በወልቃይት በኩልም ያንኑ የሱዳንን በር የማስከፈት ዓላማውን ለመተግበር ከፍተኛ ቁጥር ያለው ጦር በማሰለፍ በተለያዩ ቦታዎች ውጊያ ለመግጠም ማሰቡ ታውቋል።የአማራው ክልል መንግሥት ተብዬው የግንኙነት ክፍል ሃላፊ ግን በክልሉ ሰላም ሰፍኖ የልማት እንቅስቃሴ ተጀምሯል በማለት የተለመደ ክህደቱን ሳያፍር ደግሞታል። የወልቃይት ሕዝባዊ አስተዳደር ኮሚቴ መሪ የሆነው ኮሎኔል ደመቀ ዘውዱ ወደ አዲስ አበባ ተጠርቶ መሄዱ ቢሰማም በሌላ በኩል የሚናፈሰው ወሬ ግን የሄደው ኮሚቴውን ወክሎ ከጥቂት አባላት ጋር የፌዴራል መንግሥቱን ከባቢው የተቋረጠበት፣የባንክ፣የመብራት፣የቴሌ፣ የባጀት---ወዘተ አገልግሎቶቹ እንዲቀጥሉ ለመጠየቅ ነው ተብሏል።በሌላም በኩል ተጠርቶ የሄደው የወልቃይትን ጥያቄ

እንዲያረግቡት ትዕዛዝና ማስጠንቀቂያ ለመቀበል ነው የሚል ነው።በእኛም በኩል ይሆናል የምንለው ከዚህ የራቀ አይደለም። ኦሕዴድ ብልጽግና ከወያኔ ጋር ለሚያደርገው ስምምነት አንዱ የቀብድ መያዣ ያደረገው የራያና የወልቃይት ጉዳይ ስለሆነ ፣ከምዕራቡም በኩል የሚነሳው ጥያቄ ይኸው በመሆኑ ኮለኔሉን ለማስፈራራት አለያም ለማባበል የተደረገ ጥሪ ነው ብለን እናምናለን።ኮለኔሉ ለወልቃይት ችግር የክልሉን መንግሥት ይጠይቃል እንጂ አልፎ የፌዴራል መንግሥቱን የመጠዬቅ መብት ያለው አይመስለንም።ሌላው ደግሞ ወልቃይት በፌዴራሉ ሥር እንዲሆን፣ወይም ጉዳዩ በሕዝበ-ውሳኔ (በሬፈረንደም)እንዲፈታ ለማግባባት ነው የሚለው ነው። ይህም ወልቃይትን ከአማራው ነጥሎ ለወያኔ የመደራደሪያ ቀብድ ለማድረግ የታሰበ ክህደትበኮለኔሉና ጓደኞቻቸው የእምቢታ መልስ እንደተሰጠው ተሰምቷል።የራያና አዘቦ መሬት ተወሮ ሕዝቡ መከራውን ሲያይ ምንም ወሬ እንዳይነሳ ያደረገ መንግሥት በአማራው ኪሳራ ከወያኔ ቀርቶ ከኢጅብት ጋር ቢደራደርና ግድቡን አሳልፎ ቢሰጥ የሚገርም አይሆንም።እስከአሁንም ድረስ የወያኔና ኦነግ የጥፋት ሃይሎች በአማራው ላይ የሚፈጽሙትን ግፍና ጭፍጨፋ በዝምታ ማለፉ የዓላማ ትስስር መኖሩ ማሳያ ነው።ባይሆንማ ኖሮ ወያኔ በሰሜን፣ ኦነግ በምዕራብ፣በምስራቅ፣በመሃልና በሰሜን ሸዋ እንዲሁም በጎጃም አስፋልት መንገድ ይዞ እዬገሰገሰ፣የሰሜን ሸዋ ኦሮሞዎችን ሳይቀር እዬገደለ፤እዬዘረፈ፣እያወደመ ሰፊ ቦታዎች ሲቆጣጠርና ሲያስተዳድር በዝምታ አይታለፍም ነበር።ባሳለፍናቸው ቀናቶች ብቻ ግፈኛው ኦነግ በወለጋ ብቻ የአንድ ዓመት ልጅ ሳይቀር አፍኖ ወስዷል ፣ከሁለት መቶ ሰዎች በላይ አርዶና አረሸኖ በድናቸውን የአውሬ ሲሳይ አድርጓል፤ ሽማግሌ ቄስ አርዶ በእሳት አቃጥሏል።በጎጃም መስመር በጎሃጽዮንም 15 ልጆችን አግቶ የጠዬቀው ገንዘብ በወቅቱ ስላልደረሰው እርዶ ጥሏቸዋል።ለዚህም ከየአማራው ክልል አስተዳደርም ሆነ አብይ አህመድ ከሚመራው መንግሥት ተብዬው በኩል የተወሰደ እርምጃ የለም። አብይ አህመድ የተጠመደው በግንብ ምረቃና ተባባሪዎቹን አሰልፎ በሽርሽር ጉዞ ላይ ነው።

በዚሁ ሰሞን የአሜሪካኑ ተላላኪ ጄፍ ፒርስን ወደ ኬንያና አዲስ አበባ አቅንቶ ከመሪዎቹ ጋር ተነጋግሯል፣የንግግሩ እርዕስና ውጤት በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል የተገለጸ ባይሆንም ያው የባይደንን ፍላጎት የሚያንጸባርቅ ከመሆኑም በላይ ፍላጎቱ ካልተሟላ ሊያስቀምጥ ያሰበውን እቀባ ከመግለጽ ጋር የተያያዘ ነው ሲሉ የፖለቲካ ታዛቢዎች ይናገራሉ።አብይ አህመድ ከሥልጣኑ አይውረድ እንጂ ከጸሓይ በታች ባለውና ካለው ሁሉ ከመደራደር አይመለስም።የዚህም አይነት አቋም የነበረው የግንቦት ሰባቱ መሪ ብርሃኑ ነጋ አሁን የአብይ አህመድ የሥልጣን ሽሪካ(ተጋሪ) ስለሆነ ያሉትን ተቀብሎ እንዲያድር ከራሱ ተመክሮ፣ከግብጽ ጋር ካደረገው ስምምነት በመነሳት ከመምከር አይቆጠብም።ለዚህም ማስረጃው በዋሽንግተ ዲሲ ግብረሃይል የሚል ሰሌዳ ለጥፈው ለዓመታት ፎቶ ግራፉን ተሸክመው ያመልኩ የነበሩት የግንቦት ሰባት ጎጀሌዎች በጥቅምና በጎሳ አሰላለፋቸው ተለያይተው አንዱ የመንግሥትን ሌላው የሕዝቡን ጥያቄና አቋም ይዞ በመተራመስ ላይ ይገኛል።ይህ ትርምስ በዲሲ ከተማ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሳይሆን በሌሎቹም የአውሮፓና የፓሲፊክ አገሮች መከሰቱ አይቀርም። በደመቀ መኮንን በኩል የተሰባሰበው የዲያስፖራው ሆዳም ስብስብ በውጭ አገር ስለአማራው ጭፍጨፋ(ጀኖሳይድ) እንዳይነሳ ጭምር የማድረግ ሃላፊነት ተቀብሎ እዬተንቀሳቀሰ ይገኛል።ለኮንደሚኒዬም ቤት፣ለቦታና ለገንዘብ ስጦታ እራሳቸውን የሸጡ አይሁድ ጋዜጠኞችና አውደልዳዮች እስካሉ ድረስ ለጊዜውም ቢሆን የአብይ መንግሥት ደጋፊ አልባ አይሆንም።የጅቦቹ ጸባይ ላበላቸው ነውና ቀን አይተው ይከዳሉ እንጂ እስከመጨረሻው አይገፉበትም።አሁንም አንዳንዶቹ ሆድ አደሮች የሚፈልጉትን ባለማግኘታቸው ዳር ዳር እያሉ ነው።እነዚህን ልክስክሶች ፊት መንሳት ተገቢ ነው እንላለን።

ባለፈው ሃሙስ ፌብሩዋሪ 17 ቀን 2022 በዋሽንግተን ዲሲ ከግንቦት ሰባትና ከአብይ መንግሥት ደጋፊነት አፈንግጠው ወደ ሕዝቡ የተቀላቀሉት ግለሰቦች በጠሩት ሰልፍ ላይ ብዙ ሰው ተገኝቶ

የተቃውሞ ድምጹን አሰምቷል።ሰልፍ በመደረጉ ቅዋሜ ባይኖረንም፣መልእክት ለማስተላለፍ የተፈለገው ለችግሩ ባለቤትና አካል ለሆነው ለአሜሪካ መንግሥት በመሆኑ ውጤቱ ያው በገሌ እንደሚሆን እናውቃለን።ከሰልፈኛው በላይ የሚያውቁት ጉዳይ ነው።በእኛ እምነት የውስጡም ሆነ የውጩ የሕዝቡን ጩኸት ሊሰማና መብቱን ሊያከብር የሚችለው ተቃዋሚው ጎራ ጠንክሮና አንድ ሆኖ ሲቆም ብቻ ነው።ሰነፍና ደሃን ልጅ እናቱም ብትሆን አትወደውም፤ስለሆነም በትጥቅም በስንቅም ሕዝባዊ ሃይሉን ማጠናከር ተገቢ ነው።ስንዴ አምርቶ ለሌላው መትረፍ የሚችለው ህብረተሰብ ስንዴ ለማኝ ሲሆን ፣ለሌላው ሰብአዊ መብቱ ጥያቄ ትኩረት ያገኛል ብሎ ማሰብ ሞኝነት ነው።የተናቀና የተጠላ ከመሆን ያለፈ ከበሬታና፤ለጩኸቱም ሰሚ ጆሮ አያገኝም።ስለሆነም የተቃዋሚው ጎራ የጥቃት ሰለባ የሆነውን ወገኑን የመርዳትና የማቋቋም እንዲሁም መብቱ እንዳይደፈር፣እንዳይጠቃ ለማድረግ ሕዝባዊ ሃይሉን የመርዳት ግዴታውን በአግባቡ ይወጣ እንላለን። ከእጅ ወደ አፍ ካላለፈ ድጋፍ በተጨማሪ ተቋማዊ የሆነ በራስ የመተማመን ደረጃ ላይ እንዲደርስ የመርዳት ተግባር ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

አማራውንና የአፋሩን መነሳሳት የፈራው መንግሥት ተብዬው ጸረ ኢትዮጵያ የኦሕዴድ መራሹ የኦነግ ወያኔ ውልድ ለኢትዮጵያ አንድነትና ለመብቱ የተነሳሳውን የአማራ ፋኖና የአፋር ሕዝባዊ ሃይል ለማጥቃት እቅድ አውጥቶ ተጻራሪ ቀለብተኛ ቡድን አሰማርቶ በመንቀሳቀስ ላይ ነው።በዚህ እርምጃው ትግሉን ለመቀላቀል ያሰቡ ብዙዎች ሲታሰሩ የቀሩትም በወከባ ላይ ናቸው።

ከወለጋ ተፈናቅለው አዲስ አበባ ለመግባት የቻሉትን ዜጎች ፖሊስ እያፈሰ ለማስወጣት ሲሞክር የባልደራስ ፓርቲ አባላት ደርሰው ያስቆሙት ሲሆን የአዲስ አበባ ወጣቶችም ለተፈናቀሉ ወገኖቻቸው በጃንሜዳ ውስጥ የማረፊያ ቦታ በማዘጋጀትና ምግብና ውሃ በማቅረብ የታደጓቸው መሆኑ ተሰምቷል። እንዲህ አይነቱ ሕዝብ ለሕዝብ አጋርነት በሰፊው ቢቀጥል የጠላቶችን ቅስም ሊሰብርና የሚፈለገውን ድል ለመቀዳጀት ያስችላል።

ዓርብ ፌብሩዋሪ 18 ቀን 2022ዓም በአውሮፓ ህብረት መቀመጫ በሆነችው በብራሰልስ ከተማ የወያኔና የኦነግ ደጋፊዎች በመተባበር የተቃውሞ ሰልፍ አካሂደዋል።ወያኔና ኦነግ ሲገሉና ሲዘርፉ ድምጻቸውን ያላሰሙት የባለሥልጣኖቹ ልጆችና ቤተሰቦች ፣እንዲሁም የመኖሪያ ፈቃድ የሌላቸውን በመቀስቀስ አሁን አደባባይ ወጥተው ያዙኝ ልቀቁኝ ማለት ከዴሞክራሲ መብት ጋር የተያያዘ ሕዝባዊ ጥያቄ አንግበው ሳይሆን ከነበረን የሥልጣን ቦታ ለምን ተነቀልን ከሚል ቁጭት የተነሳ ለመሆኑ ያወርዱ የነበረው መፈክርና የሚታይባቸው ደም ፍላት ያረጋግጣል።በትግራይ ሕዝብ ላይ ለሚደርሰው ስቃይ ተጠያቂው ወያኔና ኦሕዴድ መራሹ መንግሥት እንጂ ንጹሁ የአማራም ሆነ ሌላው ኢትዮጵያዊ አይደለም።ለትግራይ ሕዝብ ከታሰበ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ጋር ሆኖ ወንጀል የፈጸሙትን መቅጣትና ወያኔንና የዘረጋውን የጎሰኞች ሥርዓት ማሶገድ ነው።

ይህ ተቃውሞ በሚካሄድበት ቦታ አብይ አህመድ ከሌሎቹ መሪዎች ጋር በቡድንና በነጠላ እዬተገናኘ ያሰቀመጡበትን እቀባ እንዲያነሱለትን የእርዳታ እጃቸውን እንዲዘረጉለት ተማጽኗል።መማጸንም ብቻ ሳይሆን የፈለጉትን ለማድረግ ቃል በመግባቱ በአሜሪካኖች ትዕዛዝ የሚንቀሳቀሰው የዓለም ባንክ 64 ሚሊዮን ዶላር ለመስጠት ቃል ገብቶለታል።አብይና የሚመራው መንግሥት ዓላማው ገንዘብ መሰብሰብ ስለሆነ የአገራችንን ጥቅም አሳልፎ ከመስጠት ወደ ኋላ አይልም። እንዲያማ ባይሆን ኖሮ የዓለም ባንክ የያዘውን አቋም ለውጦ ተንደርድሮ እረዳለሁ አይልም ነበር።

ቅዳሜ የካቲት 12 ቀን 2014 (ፌብሩዋሪ 19-2022) 85ኛው የሰማዕታት ቀን ተከብሮ ውሏል።በስድስት ኪሎ የሰማዕታት ሃውልት ዙሪያ በተከበረው የመታሰቢያ ዕለት ምንም እንኳን የወያኔ ባንዲራ

የተውለበለበበት ቢሆንም፣ የአርበኞች ማህበርና አንጋፋ  የጦር ሃይል አባላትና ከዬትምህርት ቤቱ የተውጣጡ እስካውቶች እንዲሁም የከተማው ወጣቶች በዓሉን አክብረው ውለዋል።በጣም የሚያኮራውና ተስፋ የሚጭረው፣ለበዓሉ ድምቀትም የሰጠው በወጣቶቹ የሚወርደው የፉከራና ሽለላ እንዲሁም መዝሙር ነበር።ተከብረሽ የኖርሽው ባባቶቻችን ደም፣ እናት ኢትዮጵያ የደፈረሽ ይውደም። የሚለው ወኔ ቀስቃሽ መዝሙር በወጣቱና በፖሊስ የሙዚቃ ጓድ ተስተጋብቷል።ቀጣዩን  ክብረበዓል በሰላም፣በአንድነትና በነጻነት ለማክበር ያብቃን እያልን ምኞታችንን በመግለጽ የዛሬውን የአገር እንዴት ሰነበተች ቅንብር በዚህ እንደመድማለን።

ኢትዮጵያ በነጻነትና በአንድነት ለዘለዓለም ትኑር!!

በስዊድን የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ የስነጽሑፍ ክፍል